ዝብርቅርቅ ፖለቲካ

( ታማኝ ተቃዋሚ፤ ወዳጅ እስረኛና ድርጅት ለቅርጫ)

ሀማ ቱማ

“አምስት አቦ ናቸው፤ ሰባትም ሥላሴ
ስድስትም ለቁስቋም ስምንት ለቢዮንሴ።
አስራ ዘጠኝ ገብርዔል፤ ሀያ አንድ ማርያም ናት
ሀያ ባዶ እንዳትቀር ለአላሙዲ እንስጣት።፡”

ሰውየው ለከት አልባ ካድሬ ነውና ከላይ የሰፈረውን አላለም ብሎ ለመከራከር አይቻልም። ባይለውም አስቦታል ብንል አንሳሳትም። የአባ ገብረ መድህን ወይም የወያኔው ጳጳስ ጉድ ብዙ ነውና --በተለይም የአሜሪካኗ ዘፋኝ ጉብኝት ጊዜ ስነ ስርዓት ለቆ ነበርና። አባ ገብረ መድህን በብዙ ሺ ብር ወጪ የራሱን ፎቶ በየቤተክርስቲያኑ እንዲለጠፍ አዟል። ሊጎዳቸው ያሰባቸውን ያሳብዳቸዋል የተባለውን ያስታውሰናል። የሀይማኖቱ መስክ ለወያኔ ትኩረትን ሳቢ ከሆነ ውሎ አድሯል። ሕዝብን ለመከፋፈል ከብሄረሰብ ባልተናነሰ ጠቃሚነቱን የደደቢት ባለዛሮች ጠንቅቀው ተረድተውታልና በቤተ ክርስቲያኖችና መስጊዶች ጉዳይ ጣልቃ መግባት ከጀመሩ ቆይተዋል። በየቦታው በሀይማኖት የተነሳ ግጭቶች መከሰትም ጀምረዋል። በዚህ መስክ ካድሬው ጳጳስ ቤተክርሲያኗን ከማፍረስ አንፃር ሚናው ከፍተኛ ነው። ለቢዮንሴና አላሙዲ የበዓል ቀናት ቢሰጣቸው አያስገርምም ለማለት ነው።

ወደ ቁምነገሩ መለስ ስንል ደግሞ ይህ ታማኝ ተቃዋሚ የሚለው ፈሊጥ የዘንድሮው ዝብርቅርቅ ፖለቲካ ዋና መለያ ሆኖ ይገኛል። በመሰረቱ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገሮች ታማኝ ና ተቃዋሚ አብረው የሚሄዱ ፅንሰ ሀሳቦች ሊሆኑ አይችሉም። ተቃዋሚ ድርጅት የሚመሰረተው ያለውን ስርዓትና አገዛዝ በመቃወም እንጂ ለማጻነቅና ለመደገፍ አይደለም። ለወያኔ እንደ ብአዴንና ኦሕዴድ የቀትር ጥላ ለመሆን የተመሰረተ ድርጅት ተቃዋሚ ሊባል አይችልም። ድርጅቱ ተለጣፊ ሳይሆን ተቃዋሚ ሊባል የሚችለውም ባለው ትግልና የተፃረረ አሰላለፍ በስልጣን ያለውን ተቃውሞ ሲገኝና ታማኝነቱ ለአገዛዙ ሳይሆን ለሕዝብ ወይም ለሕዝብ አንድ የተበደለ ክፍል ሲሆን ነው። ለአገዛዙ ታማኝ የሆነ ድርጅት ተቃዋሚ ሳይሆን አጃቢ፤ተቃዋሚ ሳይሆን ተለጣፊ ነው። ለዚህም ነው ታማኝ ተቃዋሚ ለመሆን ደፋ ቀና የሚሉትን ለተለጣፊነት ራሳቸውን አሰለፉ--አዋረዱ ብለን የምንተቻቸው። የወያኔ አገዛዝ ከሌባ ዓይነ ደረቅ የባሰ ነውና ህገ መንግስት ያልኩትን ተቀበሉልኝ ሲል እንኳን የአንድ ቡድንን ህግ ቀርቶ ህዝብም ያፀደቀውን ህግ የመቃወም መብት ሊገፈፍ የማይችል መሆኑን ያልተረዱ ክፍሎች እሺ እንቀበላለንን እያስተጋቡ ለአምባገነኑ ተንኮል ሰለባ ይሆናሉ/ሆነዋልም። ሀቀኛ ተቀዋሚ ገና ሲነሳ የወያኔን አገዛዝ በአጠቃላይና በተለይም ህዝብ በድምፁ ያላፀደቃቸውን ህጎችና ሰነዶች አልቀበልም ብሎ መነሳት--መቆም አለበት። ይህ ተቃውሞ እንዴትና በምን ዓይነት ይከሰታል

የሚለው ሌላ ጥያቄ ሲሆን መቀበል አለመቀበል ላይ ግን አለመቀበል ራሱ መብት መሆኑን ማስረገጡና ማረጋገጡ አስፈላጊ ነው፡፡ ወያኔ ባጠረው ጠባብ በረት ገብቶ ልፈንጭና መብት ላስከብር አይቻልምና ነው፡፡

መንግስታዊ ሶሻሊዝም የርዕዮቱን መሰረትና ተስፋ አደባይቶ የሰፊው ሕዝብ የበላይነትን በጨቋኝ ፓርቲ አምባገነንነት በመተካቱ በትግል ሲንኮታኮት ዋነኛው ሰው በዝብዝቡ ስርዓት በዓለም አቀፍ ደረጃ ገኖ የበላይነትን በመያዙ የፖለቲካና ትግል ይዘቱ የተዘበራረቀባቸው ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ሚቹ የቫቲካን ጳጳስ እንኳን ያወገዙት ጨካኝ ስርዓት ከመቅፀበት የስርየት መንገድ የሆነ ይመስል ትላንት ሰማያዊውን የፓርቲ ቱታ አጥልቀው በሶሻሊዝም ሲምሉ ሲገዘቱ የነበሩት ሳይቀሩ በካፒታሊዝም ስርዓት ደጋፊነት ተጠምቀው የበሉበትን ወጪት ሰበሩ፡፡ ያ የፈረደበት ትውልድና የግራ ሀይል ተወገዘ፡፡ ባመኑበት ፅናቱ የሳሳባቸው ደግሞ ራሳቸውን በአጥፍተናል ጅራፍ እየጠበጠቡ ሀያል ለተባለው መንግስት ሰገዱ፡፡ ኢትዮጵያም ሆነች አፍሪካ በሞላ የሚበጀው ስርዓት በየሀገሩ ተጨባጭ ሁኔታና ይዞታ መሰረት የብዙሀኑን ጥቅም አስቀድሞና ተንከባክቦ የሚገኘው መሆኑ ግልፅ ሆኖ ሳለ ከበርሊን ግንብ ጋር አብረው የፈረሱት ደግሞ አሜሪካ ወይ ሞት በሚል ለዚህ በለስ ለቀናው ጣዖት መስገዱን መረጡ፡፡ ከዚህ ቀደም የሀገራችን ተቃዋሚ ሀይሎች ለማንም ባዕድ መስገድን እምቢ ብለው ሲገኙ የዛሬዎቹ ደግሞ ያውም ለቡሽ አሜሪካ ጎንበስ ማለቱን መርጠው ተገኙ፡፡ በአሜሪካ ደረጃ እንኳን የቡሹ ቡድን የቀኝ ቀኝ ዘረኛና በዝባዥ ለመሆኑ ደግሞ ምስክር መጥራትን የሚጠይቅ አይደለም፡፡ ታዲያ የተቃዋሚ ሀይል መሪና ምሁር  ነኝ ባይ ግለሰብ አሜሪካ በዓለም ሁሉ ዴሞክራሲን ሊያሰፍን እየደከመ ነውና ለኢትዮጵያም ዴሞክራሲን ያመጣላታል ብሎ መለፈፉን ምን ልንለው ይገባል? ኢትዮጵያን ለወያኔ ቡድን አሳልፎ የሰጠና ዛሬም ለመለስ አገዛዝ ዕድሜ መራዘም ምክንያት የሆነውን በነፃ አውጪ መድቦ መገኘትስ የፖለቲካን ውል ስቶ መደናገርን አያመለክትምን?

ያመለክታል ስንላቸው ደግሞ አንድም የሰለጠነ ፖለቲካ አልገባችሁም ሲሉን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ፀረ አሜሪካ ናችሁና ቅዠት ይዟችኋል ሲሉን፣ አልፎም በተራቀቅነው ምሁሮች ቀናችሁ ሲሉን ማድመጥ ተገደናል፡፡ ክዶ ከመሟገት አምኖ መረታትን አይቀበሉምና ሁሌም ማስረዳቱ የግድ ሆኗል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ከወያኔ ስነ ስርዓትን፣ ህግ አክባሪነትን፣ ኢትዮጵያዊነትን መጠበቅና ከአሜሪካ አስተዳደር ደግሞ ፍትህና ለሀገራችን ሕዝብ አሳቢነትን መጠበቅ ከሞኝነት አልፎ የባለቤት ሰነፍ ቤቱን ያዋርዳል የሚያሰኝብን ይሆናል፡፡ ታማኝ ተቃዋሚ የተባለውን ልዩ ፍጡር ወያኔ የሚያስተናግደው አይደለምና ታማኝነትና ተለጣፊነት ተወራራሽ መሆናቸው የግድ ይሆናል፡፡ ለዘብተኛ ተቃዋሚ ወይም በጮሌው አነጋገር ስልጡን ፖለቲከኛ በሚል ሽፋን ለደደቢቱ ጣዖት ወገብ ሊሰብሩ (አቴና ወጊ፣ ወገብ ሰባቂ ያሉትን አፄ ቴዎድሮስ እናስታውስ?) የቆረጡትን ስናይ ወደዱም ጠሉም ሰልፋቸው ከሕዝብ ሳይሆን ለገዢው ክፍል በሚጠቅም ጎራ ነው፡፡ ይህን ስንል እንዲያው በጭፍን ጥላቻ ብቻ ሳይሆን ያሳለፍነው መራራ ተመክሮ ሀቅ ብሎን ነጋሪት ስለሚጎስምብን ነው፡፡ ለነገሩ ጥላቻም ሲያንስ ነው፡፡ በሀገራች ላይ ወያኔ የፈፀመውን

ከባድ በደል ብንተው እንኳን በራሱ በኢሕአፓ ደረጃ የወያኔ ቡድን ለስንት ጓዶች ውድ ህይወት መጥፋት ምክንያት ነው:: ከእነ ገመቹ እስከነ መስከረም፣ ከእነ  ገለብ እስከ ጋይም የስንት ጓዶች ደም ይጮኃል:: ይህን ትተንና ረስተን ከወያኔ እንተቃቀፍ የሚሉት ደግሞ ይካስ የበደለን እንኳን የተዉ ተጎንባሾች መባላቸው አልቀረም:: ደብዛቸው የጠፋውን ጀግኖች ከፀጋዬ ደብተራው እስከ አዛናው ደምሌ፣ ከብርሃኑ እጅጉ እስከ ስጦታውና ደምሴ፣ አበራሽ፣ ለማና ተስፋዬን ረስቶ ከአጠፋቸው ወያኔ ቡድን ጋር ተለሳልሶ መሰለፍን የሚሰብክ ሁሉ ሰልፉ ከሕዝብ ሳይሆን ከክህደት ጎራ፣ ከከርስ ፖለቲካ፣ ከተለጣፊ መንጋ መሆኑ መነገርና መወገዝም ያለበት ነው:: ሰብዕናውን የሚያዋርድ ግለሰብ ሆነ መርሁን የሚያረክስ ድርጅት ለህገርም ለራሱም መቸም የሚበጅ አይሆንም:: ከነፍሰ ገዳይ ጋር በወንድሙና እህቱ ሬሳ ዙሪያ ጉሮ ወሸባዬ የሚለው ከፊሪነት ባሻገር ብርክ የያዘውና ለገዳይ የሚያረግደው መፍራት በሌለበት ሁኔታ ከሆነ ደግሞ የሞት ሞት ውርደትና ቅሌት ነው::

ይህ የተምታታና የተዘበራረቀ ፖለቲካ ቅጥ አምባሩ ጠፍቶት የአባቴን ገዳይ አባባ አልኩት ዓይነት ወዳጅና ጠላትን መለየት አቅቶት ሲደናበር ለመታዘብ ተገደናል:: በሕዝብ ላይ ወንጀል የፈፀሙትን አለምንም ንስሃ ወይም ግለሂስ ጀግና ብሎ ማቀፉን የሚሰብኩ ብዙ ናቸው:: የሰለጠነ ፖለቲካ የሚባለው በህሊናና በአንጎል ላይ መተኛት የሆነ ይመስል የደረሰ በደልን በደለኛው አጠፋሁ ባይልም እርሱለት የሚሉ በዝተዋል:: ማን ይጩህ የቆሰለ ነውና ያልደረሰባቸውና ያልተጎዱ በደፈናው እርሱት ቢሉ የሚገርም አይደለም:: በሰው ቁስል እንጨት መስደድ ቀላል ነውና:: ከመለስ አገዛዝ ተጣላን ላሉት የወያኔ መሪዎች  ጆሮ ሰጥቶ ሕዝቡ ቢጠብቅ ያገኘውና መስማት የተገደደው የአረና ቅሌትን ነው:: መለስን ተጣላን ባዮቹ ዛሬም በልባቸው በወያኔ ቃል ኪዳን አምነው የወያኔን መርህና አቅዋም ተቀብለው ( ያላመኑ ካለ ፕሮግራማቸውን ያንብ) በጠባብ ሰልፋቸው ፀንተዋል:: ትላንት ጦርነት እንሰራለን ፣ ወዲ ትግራይ እያለ ማነው የሚሾም የሚሸለም ሲለን የነበረውና በዕብሪት በኢትዮጵያ ላይ ሲፏልል የነበረውንም ግለሰብ አለምንም ቅድመ ሁኔታ አቅፈው ጀግና የሚሉት በአደባባይ ታይተዋል:: ከጠላት የተጣላን በደፈናው ወዳጅ ማለቱ ባይገባም ማስተናገዱ ይጠቅማል የሚባለው ተጣላሁ ባዩ በመሰረቱ ጠላት ካልነው ከተጣላ ነው:: መለስ ይወገድ ግን የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ይለምልም ባዮች የሕዝብ ትግል አጋሮች አይደሉም:: ሊወድቅ ያለውን አገዛዝ በአዲስ መልክ ዕድሜ ሊቀጥሉለት የሚራወጡ ናቸውና ከሕዝብ ትግል አንፃር ለነፃነታችን ጠር ናቸው:: በወንጀል የተሳተፉና ከአምባገነናዊ አገዛዝ አካል ሆነው በደል የፈፀሙ እንደ በግ እንኳን ባ ወይም ይቅርታ ሳይሉ ወደ ሕዝቡ ጎራ ሊደባለቁ አይችሉም:: ይደባለቁ ማለቱ ደግሞ ቻይነት ወይም የፖለቲካ ብልህነትን ሳይሆን ዳግም መጃጃልን አመልካች ነው:: በሀገር ደረጃ ደግሞ የጠላነው አገዛዝ በአዲስ መልክ ሊቀጥል መፍቀድ ማለት በሀገርና በሕዝብ ላይ ወደድንም ጠላንም ከፍተኛ በደል መፈፀም ነው::

እውነቱ ይነገር ከተባለ ደግሞ ስብሀት ነጋ ነገ ከመለስ ቢጣላ የሕዝብ ወገን ሆነ ማለት አለመሆኑን መርሳት አይገባም፡፡ እነ ገብሩ አስራት ሆኑ እነ ስዬ አብርሃ ከመለስ ዜናዊ ጋር ሆነው ሀገራችን ለደረሰባት አሰቃቂ በደል ተጠያቂ ናቸው፡፡ ይባስ ብሎ ዛሬም የሚናገሩት ይቅር በለን ሕዝብ ሆይ ሳይሆን በትግራይ ማንም አይምጣብን፤ ኢሕአዴግ ጤነኛ ነው፤ ወያኔን አትዋጉት፤ ዕርቅ ወሰላም (አበራ የማነአብ ምን ይል?)፤አንቀፅ 39 ወይ ሞት ወዘተ የሚል ነው፡፡ ከመለስ ጋር ሆነው ስላጠፏቸው እስረኞች የሚያወሩትም የለም፡፡ የወያኔን ምስጢር ምስጢራቸው አድርገው ይዘዋል፤ደብቀዋል፡፡ የሰላማዊ ትግልና የዕርቅ ሰባከቸው ደግሞ አገዛዙን ለማዳንና የጠባብ የበላይነትን ለመቀጠል (ካስፈለገ መለስ ተወግዶ) መሆኑ ሊደበቅ የሚችል አይደለም፡፡ ይህን ሁሉ ዘንግተው፤አላይ ብለው፤ ወይም ለከርስ ፖለቲካ ተገዢ በመሆን ስለእነ ስዬ ጀግንነት ሊያወሱና ሊያዳንቁ፤ ተሰብሰቡለት ሊሉ ኡኡታ የሚያበዙትን ብንታዘብ ሲያንስ ነው፡፡ ተጨፈኑና ዳግም ልናሞኛችሁ ፍቀዱልን ለሚሉት ደግሞ እምቢ ስንል በጣልቃ ገብነትና በቂመኛነት የሚከሱንን መከራ መክሮናልና ጆሮ አንሰጣችሁም እንላቸዋለን፡፡ የሀገርን የነገ ዕጣ በተመለከተ፤ የህዝብን ጥቅም በተመለከተ ጎጂና ተፃራሪ አቅዋሞች ሲከሰቱና ሰባከዎች ሲስተጋቡ መቃወም መብታችን ብቻ ሳይሆን የዜጋ ግዴታችን ነው፡፡ ለምሳሌ ምንም ለውጥ ሳይኖር በመጪው ምርጫ ወያኔን እናጅበው ማለቱ የሕዝብን ትግል ይጎዳል ባይ እስከሆንን ድረስ መልዕከታችንን ማስተጋባት ግዴታችን ነው፡፡ እነ አጅሬ ይቀየማሉ የሚለው ሳይሆን ዋናው ቁም ነገር የሕዝብን ትግል ይጎዳል ወይም አይጎዳም የሚለው ነው ጭንቀታችን መሆን ያለበትና ነው፡፡

ዝብርቅርቅ ፖለቲካ ነውና ማን ሀቀኛ ፖለቲከኛ ማን መሳቂያ መሳለቂያ የሚለውም ተምታቷል፡፡ ፖለቲካ አላወቅም፤ የፖለቲካ ድርጅትም አባል አይደለሁም እያሉ በመቀጠል ግን የፖለቲካ ፖለቲካ ያውም ዝብርቅርቁ የወጣበትን የሚያሰሙን ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ፖለቲካ የምርጦች ስራ ነው የሚለውን ብንቃወምም ቅሉ ሳገሩ ፊደል እንግዳ ለእናቱ ቋንቋ ባዳ የሆነው ደግሞ የሰንበት ሰባኪ ይሆናል ማለት አይደለም፡፡ በሆነ መስክ ታዋቂነትን ያተረፈ ወይም አዋቂ የተባለ ወይም ከየጎራው በእነ አዜብ ጎላ ሳይቀር በሚገኘው ዲግሪ ወይም የክብር በሚል በቱጃሩም በዘፋኙም በሚገኘው ዶክተርነት የተነሳ ሁሉም ፖለቲካኛ ወይም የፖለቲካ አዋቂ ተብሎ ፖለቲካውን ሊያዘባርቅ ፍቃድ ስለተሰጠው የሚያዝ የሚጨበጠው ጠፍቷል፡፡ ግርግሩም ሞቅ በማለቱ የፖለቲካ መሀይሞች የፖለቲካ ሊቆች ነን ብለው መድረከኑም አጣበዋል፡፡ ዛሬ በዚህም በዚያም እየተቹና እየተተቹ ያሉ ፓጮች፤ ዘፋኞችና መሰሎቻቸው ለዚሁ ምሳሌ ናቸው፡፡ ሞያ አለኝ ያለው ነገር ብቻ ሆነና ችግሩ ተባባሰ እንጂ አልቀነሰም፡፡ አስታራቂ ነን ብለው እጅ ሰጥታችሁ እንደ ሻይ ቤት ፎጣ ሁኑ የሚሉትና አገዛዙ አይቻልም በሚል መንበርከክን የሚሰብኩ የጊዜው ሐዋርያ ነን የሚሉበት ዕድል አገኙ፡፡ ትላንት ለኢሠፓ ታማኝ ሎሌ ነን ይሉ የነበረት ደግሞ ዛሬ ለመለስ አገዛዝ ታማኝ ተቃዋሚ ለመሆን ጎንበስ ጎንበሰ አሉ፡፡ ታማኝነትንም ለማረጋገጥ የወያኔ ጠላቶችን መንከስና ማንኳሰስን ተያያዙት፡፡ ለሽንፈት እጅ አልሰጥ ያሉትም በአምባገነንነትና ሌላም ተወግዘው አልፎም ትላንት ሲመሰገኑ እንዳልነበር ሁሉ ሀገሪቷን የጎዱ ተብሎ ሊወገዙ በቁ፡፡ ዝብርቅርቅ ያለውም ሁኔታ ትከሻቸው ላበጠ

የፍየል ወጠጤዎች አመችቶ ያበደች ጋለሞታ እናቷን ትመታን አስከተለ ። እነ ዶክተር ታዬ የሕዝብ ጠላት እነ ኢሳያስ አፈወርቂና ዳውድ ኢብሳ የሕዝብ አጋር ሲባሉም ለማድመጥ ተገደድን።

በዚህም በዚያም ሲታይ የፖለቲካው መዘበራረቅ የራሳችን ድክመት ውጤት መሆኑ የሚካድ አይደለም። ወያኔ የስልጣን ጉዳይ ነውና ፖለቲካውን ማደፍረሱ ተልዕኮው ነው። የሕዝብ ወገኖች ነን ያልነው ግን ፖለቲካው ጥርት ብሎ ወዳጅና ጠላትን ለይቶ መጓዝ ሲገባን በአድርባይነት፣ ለቀቅተኛነት ወይም ቸልተኛነት በመያዝ አስመሳዩ ሲደባለቅ፣ ሰርጎ ገቡ ሲደባለቅ፣ ወግድ ማለትና ማጋለጥ አልቻልንም። ዝምታ የማይበጅ ሆኖ ሳለ ድመት መነኮስኩ ባለች ጠባይዋን የተወች እየመሰለን ተሞኘን። የፖለቲካውን መድረክ ለከሀዲዎችና ለሆድ አምላኪዎች ተውልናቸው። እነሱም ያለፈውን አታንሱ፣የምን ሂሳብ ማወራረድ፣ የምን ሕዝብን ይቅርታ ጥየቃ እያሉ ባደጉበት ቀጠሉ። በመድረክ ሲኮምኩ የተሳቀላቸው በመሆኑ በፖለቲካው መድረክ የቆጥ የባጡን ቢያወሱ ሕዝብ የሚያጨበጭብላቸው መሰላቸው። አጨበጨበላቸውም። ሰባት ዓመት እንዳይማሩ ሰባ ዓመት ይደናቆሩ ተባለብን። የዘመነ ደርጉ ሳይበቃ፣ የወያኔ የራሱም ሳይበቃ ተመክሮ እንዳነሰው ሕዝብ ለአስመሳዩና ሆዳሙ ሰለባ በመሆን የጭቆና ቀንበራችንን አከበድነው። ለወያኔው ሎሌ የማይገባውን የአድናቆት ቅዕል እየለጠፍንለት ምራን ወደ ገደል ስንል ባጀን። ገደል ሲያደርሱን ኡኡታውም የሚፈይድ ሆኖ አልተገኘም። ተበልጠናልና ገና ከጠዋቱ። በዚህ መልክ ለተፈፀመው ስህተት ሁሉም ተጠያቂ ነው። ለከሀዲዎች የሙገሳ ቅዕል ለጥፎ ሲያዳንቅና ሲያደናግር የባጀው ሁሉ ሀላፊነት አለበት። ታሪኩን የረሳ ስህተቱን ይደግማል ተብሏል-- ስህተተን ፈፅመን ደግሞ በህይወት ለመገኘታችን ዋስትና የለም። ሀገራችን አለመጥፋቷ ላይ ማረጋገጫም የለንም። በደም የተገበየውን ትምህርት አንቀስምም ብለን ዳግም ብንደማ ማን ሊያዝንልን?

የምናውቀው ፖለቲካ ማለትም ዛሬ ነቃን መጠቅን ሊሉን በሚከጅሉ የእናታቸውን ተዝካር በሊታ አልሰሜዎች የፋራ ቢባልም አንጎልን በሆድ እስካልተካን ድረስ ዝብርቅርቁ ፖለቲካ በይዘቱ ወያኔያዊ መሆኑን መካድ የሚቻል አይደለም። ወዳጅ እስረኛ ተፈጠረ ብሎ ያሳቀኝ አንድ ዜጋ ቁም ነገር ነግሮኝ እንደነበር ልዘነጋም አልቻልኩም። በእኛ ጊዜ እስረኛ ሲባል በከርቸሌና በማጎሪያዎች የሚሰቃይ፣ የትኋንና ቁንጫ ሰለባ፣ ረሀብና ጹላ እራቱ፣የታረዘና የተጠማ፣የተሰቃየ እስረኛ ማለት ነበር። በደርጉም ዘመን ለነበረው ስየልና ስቃይ ዋና መስካሪዎቹ ቢያልቁም ዛሬ ቁሰልና ጠባሳውን የያዙት ሌሎች ምስክር ናቸው። በወያኔም ቢሆን የጉድጓድ እስር ቤቱ፥ ዴዴሳና ዝዋዩ ወዘተ የስቃይ ማዕከሎች ሆነው የሚገኙ ናቸው። በመሀሉ ግን ወዳጅ እስረኛ የሚባለው ብቅ አለና ለይስሙላ ታስረው የሚፈቱና የሕዝብን ጎራ ተደባልቀው የወያኔን ተልዕኮ የሚያሚሉ ተበራከቱ። ለነገሩ ዘዴው አዲስ አይደለም። ሰላይን ደብድቦ ከታሰሩት ጋር መደባለቅና ወዳጅ መስሎ ስለላውን እንዲቀጥል ማድረግ ዛሬ የተዘነጋ ቢመስልም የተለመደና የተበላም ዘዴ ነው። ወዳጅ እስረኛ የተባለው በእስር ቤት ሳይሆን ማታ ማታ ቤቱ ያድራል።

በእስር ላይም የሚደርስበት እንግልት የለም። አንዱ መሰል እስረኛ እንደነገረን ከሆነማ ሙዚቃ ማዳመጫ አይ ፖድ መሳሪያ ሳይቀር/ ነፃ የተባልነው የሌለንን/ ይፈቀድለታል። ወዳጅ እስረኛ የተባለው  እስረኛ የሚለው ፈዞለት ወዳጅ የሚለው ይጠበቅለታል። በቅጡ ያልታሰረው በይፋ ሲፈታም ከወያኔ ጋር እንታረቀ፤ይቅርታ ያድርግልን፤ አብረን እንስራ ቢል ምኑ ያስደንቃል? በጥቅሉ ስናየው የዛሬና የትላንት የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ይዞታ ለየቅል ነው። በሰለጠነ ፖለቲካ ስም ጠላትን መጥላቱ በፍራነትና ቂመኛነት ተፈርጆ ተወግዟል። ከጠላት መተቃቀፉ፤ በንግድና በጥቅም መተሳሰሩ ተወዷል። በጠላት ላይ ማዕቀብ ሲባል ወለም ዘለሙ ብቅ ይላል። በብልህነት ሽፋን አቅምን እወቅ ሰበካው እጅ መስጠትን ያቀነቅናል። አረመኔው አገዛዝ ያለውን አፀያፊ ገፅታ ጥሩ ቀለም ለመቀባትም ጥረት አለ ። ግብዙን አምባገነን አንቱ በሉት ባዮችና ወያኔ ሲባል እየሰቀቃቸው ኢሕአዴግ የሚሉቱ ሁሉ በመሰረቱ በጠላት ላይ መጨከኑ ከጥቅማቸወና ፍላጎታቸው የሚጋጭባቸው ለመሆናቸው ክርክር አያሻውም። ደብዛቸው የጠፋውን እነ ፀጋዬ ደብተራውን የምናስታውሰውና ወዳጅ እስረኞች የነበሩት ስለ አገዛዝ ጨካኝነትና ሰብዓዊ መብት ረገጣ ተመሳሳይ ግንዛቤ ባይኖረን የሚያስገርም አይሆንም። ወዳጅ እስረኛና ታማኝ ተቃዋሚ በወያኔ መዝገበ ቃላት ያሉ ለሕዝብ ባዕድ የሆኑ ፅንሰ ሀሳቦች ናቸው።

የወያኔ አገዛዝ ይዞታ በመጠኑም ቢሆን ለወጥ ባለ ፤ ያገጠጠጠ ሰውና ሀገር በላ ጥርሱ ዶልዶም ባለ ኖሮ መለሳለስን መቻቻልን ለማሰብ በተቃናጣን ነበር። ወያኔ ግን የናቅፋና ደደቢቱ ፀረ ኢትዮጵያ ዛር ለቅንጣትም ለሰኮንድም ያልለቀቀው ነው። ሀገርን መሸንሸን ብሎ በተነሳው መንፈስ ገፍቶ ዛሬ ድርጀቶችንም ለቅርጫ አቅርቦ ሲሸነሽን የሀገር ጉዳይ ባይሆን ኖር እያሳቀን ነው ባልን ነበር። ለየሕዝብ ድርጅትና ተቋም መንትያውን በተለጣፊነት እየፈጠረ እንዳለ የሚታይ ነው። በቅርቡ በአዲስ አበባ ለአንደኛው ተለጣፊ ቅንጅት የሚለውን ስም ሲለግስ ለሌላው ደግሞ የሁለት ጣት ምልክትን ሰጥቷል። የቅንጅትን ፕሮግራም ለማን እንደለገሰ ግልፅ ባይሆንም ይህ ቅርጫው ግን ወያኔ አንጃ እየቀፈቀፈ ድርጅቶችን ለመከፋፈል መራወጡን ያመለክታል። የስጋ ቅርጫ እንዳይገባ በሬና በግ ተወዶ የስጋን ጉዳይ አስቦ ማደር ይበጃል ተብሏልና ወያኔ ድርጅቶችን በቅርጫ እየከፋፈለ ማዳረሱ (ስሙ ላንተ፤ ምልክቱ ላንተ ፤ በሚል) በጣም አስገራሚ አይደለም። የሚሸነሽን ካለ ወያኔ “አለና!” ባይ ለመሆኑ ህዝብን በብሄረሰብ፤ በቋንቋ፤በሃይማኖት፤ በጎጥ ወዘተ ሲከፋፍል ወይም ሊከፋፍል ሲሞክር ያየነው ነው። ድርጅቶችንም እንዲሁ። ለዚህ ሰለባ ሆነው የሚገኙ ድርጅቶች በቅድሚያ ድክመቱና ስህተቱ የራሳቸው ነው። ራሳቸውን ከሆድ አምላኪዎች፤ ከአንጃኞችና ጨለምተኞች ማፅዳት ነበረባቸውና። ፖለቲካው የሀገርና የሕዝብ ጉዳይ ነውና ለባልተኞችና ለወያኔ ሰርጎ ገቦች ወይም ለባዕድ ቅጥረኞች ዝግ ነው ማለት ነበረባቸውና። ወርቁንም ሚዛኑንም እንዴት ልናጣው ቻልን ማለትም ይገባናል።

ዝብርቅርቅ ፖለቲካ በተለይም የራስን ሰብዕናና ክብር ከማጣትና ሀገርንም ለባዕድ ተገዢና ዝቅተኛ አድርጎ ከመውሰድም ይመጣል፡፡ ሀገሩን ያላከበረና ያልወደደ ለሀገሩ አይዋደቅም፡፡ በአገልግል ተከሽና ወደ አሜሪካ በምትሄድ ሙት ዶሮ የሚቀናው ከበረከተ ጉዳችንና መዘዛችን ገና ነው፡፡ የሀገርን አናንቆ የፈረንጁን የሚያወድስ ከበዛ ቀንበራችን ከጫንቃችን አይወርድም፡፡ ነፃነታችን ከትግላችንና መስዋዕትነታችን ሳይሆን ከፈረንጅ በጎ ፍቃድ ከጠበቅነው ተገዢነታችን ማብቂያ አይኖረውም፡፡ የራሳችንን ታሪካዊ ህገ ልቦና ንቀን ለባዕዱ ቀኖና ከሰገድን መጨረሻችን ከቶም አያምርም፡፡ ግራ ተጋብተን ስንባዝንና ከእስረኛም ወዳጅ እስረኛ ከተቃዋሚም ታማኝ ተቃዋሚ ሆነን ድርጅታችንን ወያኔ ለቅርጫ ሲያቀርብ በምፀት ማየት ከተገደድን በስህተተም በእብደትም መከሰሱ ሲያንሰን ነው፡፡ አንድ የቀድሞ ገጣሚ እንዳለው

“ ማወቅ ምን ዋጋ አለው መልኩን ካልለወጠ
ዕምነት ምን ያደርጋል ፍቅርን ካልገለጠ
ልሳንስ ምንድነው እውነት ካላሼተ
ከተንሸራተተ ከወሸካከተ ፡፡”

መወሸካከቱና፣ ማጎብደዱ፣መከፋፈሉና መዘበራረቁ አክትሞ ለሕዝባችንና ለኢትዮጵያችን ለመቆም እንብቃ፡፡